**ORIGINAL ARITICLE**

# በጎንደር ከተማና አካባቢ በሚገኙ የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ቅመማ፣ አዘገጃጀት፣ በሽታ የመለያ ዘዴና አሰጣጥ ትንተና

**ሐብታሙ አቃናው**[1]


## አጠቃሎ

ባህላዊ ህክምና በስሩ በርካታ የባህል መድሃኒት ዘርፎችን ያቅፋል። በተለይ ከባህላዊ መድሃኒት ዘርፍ ውስጥ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል። ባህላዊ መድሃኒት ከጥንት ጀምሮ ዛሬም ድረስ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ በህክምናው መስክ ከፍተኛ የሆነ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሀገረሰባዊ የዕውቀት ዘርፍ ነው። ጎንደር ከተማም ቀደም ባሉት ዘመናት የስልጣኔ፣ የፖለቲካ፣ የንግድ፣ የሃይማኖታዊ ትምህርት ቤቶች መነኻሪያ እና የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ሆና በመገኘቷ ምክንያት የባህላዊ መድሃኒት ዕውቀቱ ያላቸው ሰዎች በቤተክርስቲያን በኩል ለተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራት ወደ ከተማዋ በመግባታቸው የባህላዊ መድሃኒት እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም "በጎንደር ከተማና አካባቢ በሚገኙ የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ቅመማ፤ አዘገጃጀት በሽታ የመለያ ዘዴና አሰጣጥን" አጠቃላይ ሁኔታ መመርመር ነበር። የጥናቱ ተሳታፊዎች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ የተመረጡ በጎንደር ከተማና አካባቢ የሚኖሩ ስምንት ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አዋቂዎች ናቸው። እነዚህ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ የተመረጡትም ስለ ባህላዊ መድሃኒት ከፍ ያለ ዕውቀትና የተሻለ መረጃ ያላቸው በመሆናቸው ነው። ከእነዚህ የጥናቱ ተሳታፊዎች መረጃ የተሰበሰበው ደግሞ በተሳትፏዊና ጽሞናዊ ምልከታዎች እና በቃለመጠይቅ ነው። ጥናቱ በተግባራዊ የትውር ንድፈ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴ የቀረበ ነው። የተገኙት መረጃዎችም በይዘትና ገላጭ የመረጃ የመተንተኛ ዘዴዎች ተተንትነዋል። በጥናቱ ሂደት ባህላዊ ሃኪሞች ከተለያዩ የዕፅዋት ዓይነቶች ባህላዊ መድሃኒት ለማዘጋጀትና ተገቢውን የባህል መድሃኒት ለህሙማን ለመስጠት የበሽታውን ዓይነት ባህላዊ በሆነ መንገድ እንደሚለዩ ለማረጋገጥ ተችሏል። የበሽታውን ዓይነት ከለዩ በኋላም የመድሃኒት ዕፅዋቱን ለመሰብሰብ አንድም ከዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ አንድም ከመኖሪያ አካባቢያቸው ካላመዷቸው ዕጽዋቶች፣ አንድም ዕፅዋቱን በመግዛትና ከሌላ ባህላዊ ሃኪም ጋር በመለዋወጥ የሚያገኟቸውን የመድሃኒት ዕፅዋቶች ይጠቀማሉ። ዕፅዋቱን በመሰብሰብ ሂደትም ለባህላዊ ዕፅዋት መቁረጫ፣ ስር መቆፈሪያና ማዘጋጃ (መቀመሚያ) የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎችና ዕፅዋቱ ለተገቢው ዓላማ እንዲሰምር ሲባል የሚደረግ የዕፅ ማንገሻ ጸሎት አላቸው። በተጨማሪም የባህላዊ መድሃኒት ዕፅዋቱን ከመገኛ ቦታቸው ለመሰብሰብና የመድሃኒቶቹን ፈዋሽነት ለማጠናከር የሚያገለግሉ የተለያዩ ልማዳዊ ድርጊቶች ወይም ሃገረሰባዊ ክዋኔዎች ይከወናሉ። በዚህ ጥናት የተካተቱ የመረጃ አቀባዮች ዕምቅ የሆነ የባህላዊ ዕፅዋት መድሃኒት ዕውቀት ባለቤቶች ሲሆኑ፣ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቱን ዘመናዊ በሆነ መንገድ የሚሰራበት ሁኔታ በሚመለከተው አካል ቢታሰብበት አሁን በህክምናው መስክ ያለውን ዕድገት ወደ በለጠ ደረጃ ሊያሻሽለው የሚችል መሆኑን እና የዕፅዋት መድሃኒቱንም ከመጥፋት መታደግ እንደሚገባ ጥናቱ ይጠቁማል።


**ቁልፍ ቃላት፡** -የዕፅዋት መድሃኒት፣ ቁሳዊ ባህሎች፣ ትዕምርታዊነት፣ ምስጢራዊነት፣ የዕፅ ማንገሻ ጸሎት፣ ሃገረሰባዊ ክዋኔ፣ የቀንድ ካራና የወይራ አንካሴ፤

## መግቢያ

**ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ወይም ሀገረሰባዊ የዕፅዋት መድሃኒት የሚባለው የባህል ህክምና ዘርፍ ከፎክሎር ጥናት መስኮች ውስጥ በሀገረሰባዊ መድሃኒት ስር የሚፈረጅ ሰፊ የሆነ የፎክሎር የጥናት መስክ ነው። እንደ** Young፤(1970፣24)**ገለጻ፣ ባህላዊ መድሃኒት የሚባለው ዕፅዋትን፣ እንስሳትን፣ ማዕድናትንና መንፈሳዊ የፈውስ ስርዓቶችን መሰረት ያደረገውን በሽታን ለመፈወስ፣ ጤናን ለመጠበቅ፤ ለማከምና ለመከላከል ሲባል የሚከወንን ማንኛውም ባህላዊ የህክምና ተግባር፣ ዕውቀትና እምነትን የሚመለከት ነው።** Alemayehu(1984፣124)**እንዲሁ ስለባህላዊ መድሃኒት ሲገልጹ፤ ባህላዊ መድሃኒት የሚባለው ማህበረሰቡ ከጥንት ጀምሮ ከተለያዩ የበሽታ ዓይነቶች ለመፈወስ ሲባል የሚውለውን ማንኛውም የባህላዊ መድሃኒት ህክምና ዓይነት ነው፣ ይላሉ። ተመስገን**(2003) **እና** National Center for Farmworker Health(2011)**ደግሞ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት፣ መንፈሳዊና ተግባራዊ ክዋኔዎች አማካይነት የሚደረገውን ባህላዊ የበሽታ ፈውስ ስርዓትና ከባህላዊ የበሽታ ፈውስ ስርዓት ጋር ያሉ እምነቶችንና አመለካከቶችን አጣምሮ የያዘ የማህበረሰብ ልማድ እንደሆነ ይገልጻሉ።**

WHO(2002.፣6-7) **ባህላዊ መድሃኒት የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ በተመለከተ ሁሉንም ሊያስማማ ይችላል ያለውን**

1 **ጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ ማህበራዊ ሳይንስና ስነ ሰብዕ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች)ና ስነ ጽሑፍ- አማርኛ ትምህርት ክፍል ፖ. ሳ. ቁ.** 196 Email Adress: habtamugeb@gmail.com Gondar, Ethiopia

የሚከተለውን ተግባራዊ ብያኔ ሰጥቷል፡፡

> ባህላዊ መድሃኒት፣ ከተለያዩ ተፈጥሯዊ ነገሮች ማለትም ከዕፅዋት፣ ከእንስሳትና ከማዕድናት የሚዘጋጁ የተለያዩ ባህላዊ መድሃኒቶችን የሚያጠቃልል ዘርፍ ነው። በተጨማሪም ባህላዊ መድሃኒት መንፈሳዊ ህክምናን፣ የእጅ ህክምና ስልቶችን፣ በሽታን ለመከላከልና ጤንነትን ለመጠበቅ በግለሰብ ደረጃ ሆነ በቡድን የሚደረጉ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ለህመምተኛ የሚደረጉ እንክብካቤዎችንና ድጋፎችን፣ አካላዊ ምርመራዎችን፣ ህመምን ለመከላከል የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ሁሉ ያጠቃልላል።

ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት የሚለው የፎክሎር የጥናት መስክ ብዙ ጊዜ በባህል መድሃኒት አዘገጃጀት ሂደት ከሌሎች የባህል መድሃኒት ዓይነቶች ጋር እየተቀላቀለ የሚዘጋጅ በመሆኑ የተለያዩ መጠሪያዎች አሉት፡፡ Fekadu(2001፣ 1-2) እና Abera (2003) ባህላዊ መድኃኒት በተለያየ ስያሜ ስለመጠራቱ፡- "ባህላዊ መድኃኒት እንደአቀማመጡና አተገባበሩ እንደ ከዋኙ ማኅበረሰብ ባህል፣ ልማድ፣ እውቀት፣ ጥበብና ፍልስፍና ልዩ ልዩ ዓይነት መጠሪያና ስያሜዎች ያሉት ሀገር በቀል የህክምና ዘርፍ ነው፤ በማለት ሲገልፁ Sofowora(1982) ደግሞ በበኩሉ ሀገረሰባዊ መድሃኒት፤ አማራጭ መድሃኒት፣ ባህላዊ የዕጽዋት መድሃኒት፣ አጋዥ መድሃኒት፣ ውልቃትና ስብራትን፣ የጡንቻ መሸማቀቅን፣ ወለምታና ሌሎችን በወጌሻ የማዳን ጥበብን ያካተተ፣ ሀገር በቀል መድሃኒት በሚሉ የተለያዩ ስያሜዎች እንደሚጠራ ይገልጻል።

በተጨማሪም ተመስገን(2003፣ 22-24) እና መስፍን(2003) ባህላዊ መድሃኒት አማራጭ መድሃኒት በመባል እንደሚጠራና በስሩም ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒትንና ሌሎች በርካታ ጉዳዮችን ያቀፈ እንደሆነ ይገልጻሉ። ከዚህ በላይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት የሚቻለው፤ ባህላዊ የዕፅዋት መድኃኒት ከተለያዩ የዕፅዋት ተዋጽዖዎች የሚዘጋጅ፣ የሰው ልጅ ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ በሽታን ለመከላከል፣ ከህመም ለመፈወስ፣ አካላዊ፣ አዕምሯዊና ስነልቦናዊ በሽታዎችን ለማስወገድ ሲል የሚተገብራቸው የባህላዊ የህክምና ስርዓትና ከስርዓቱ ጋር ያሉ እምነቶችንና አመለካከቶችን አጣምሮ የያዘ የማህበረሰብ የዘመናት ጥበብ፣ ልማድ፣ ተሞክሮ እና እውቀት ውጤት መሆኑን ነው፡፡

## በባህላዊ ህክምና ባህላዊ በሽታን የመለያ ዘዴ

የባህል መድሃኒት ዘርፈ ብዙና ውስብስብ ነው። ዘርፈ ብዙና ውስብስብ በመሆኑ ምክንያት ለተለያዩ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ አእምሯዊ፣ ማህበራዊ እና መሰል ውስብስብ ችግሮች ሊዳርግ ይችላል፡፡ ስለዚህ በባህል መድሃኒት ህክምና የመድሃኒቱን ምንነት ማወቅ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱን የበሽታ ዓይነትና ለበሽታውም ተገቢ የሆነውን ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ማንነት ለይቶ ማወቅን የሚጠይቅ ትልቅ ተግባር ነው።

ባህላዊ ሃኪሞች ባህላዊ መድሃኒቱን በመሰብሰብና በማዘጋጀት ለበሽተኛው ለመስጠት በቅድሚያ ባህላዊ በሆነ መንገድ የበሽታውን ዓይነት ከለዩ በኋላ የባህላዊ መድሃኒት የዕፅዋት ግብዓቶችን ማሰባሰብ ይጀምራሉ፡፡ እንደ Young(1970)፣ Konadu(2007)፣ ተመስገን(2003) እና Sofowora (1982፣26-28) ገለጻ የተለመዱ የበሽታ መለያ ዘዴዎች የሚባሉት ዕይታዊ ምርመራ፣ ክሊኒካዊ ምርመራ ፣ ባዮሎጂካዊ ምርመራ እና ህመምተኛውን በአትኩሮት በመመልከት መለየት እንደሆኑ ይገልጻሉ።

ክሊኒካዊ ምርመራ ሰፊ ክፍል የሚሸፍንና ከዘመናዊው የምርመራ ዘዴም ጋር የሚመሳሰል ባህላዊ የበሽታ መለያ ዘዴ ነው። ክሊኒካዊ ምርመራ ልክ እንደዘመናዊው የህክምና የምርመራ ዘዴ ሁሉ የህመምተኛውን አካላዊ ሁኔታን፣ የልብ ምትን፣ የተለያዩ የመገጣጠሚያ አካላት እንቅስቃሴን፣ የሰውነት ሙቀትን፣ የጅማት ከቦታ መልቀቅን፣ የአጥንት መሰንጠቅና መሰበርን፣ የመገጣጠሚያ አካል ውልቃትን፣ የክብደት መቀነስን፣ የላብ ሁኔታን፣ የሆድ ቁርጠትን፣ ማሳከክን እና የመሳሰሉትን ምልክቶች መሰረት በማድረግ በሽታ የሚለዩበት ስልት ነው።

ባህላዊ ሃኪሞች በሽታን ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚለዩበት ሁለተኛው ዘዴ ዕይታዊ ምርመራ ነው። እንደ Sofowora(1982፣26-28) ገለጻ፤ ዕይታዊ ምርመራ ባህላዊ ሃኪሙ የህመምተኛውን ዓይን፣ ቆዳ፣ ሽንትና ዓይነምድር በመመልከት እና በመፈተሽ የህመሙን ዓይነት ለመለየት የሚጠቀምበት ዘዴ ነው። ሶስተኛው ባህላዊ የበሽታ መለያ ዘዴ ሆኖ የሚያገለግለው ባዮሎጅካል ምርመራ ሲሆን ይህ ስልት የባህል ሐኪሞች የስሜት ህዋሶቻቸውን በመጠቀም በማሽተት፣ በመዳሰስ ወይም በመንካትና በማየት የበሽታውን ዓይነት የሚለዩበት መንገድ ነው። በተጨማሪም የህመምተኛውን የምግብ ፍላጎት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የሕመሙን ሁኔታ፣ የመንስኤ፣ ምክንያትና ሌሎች የበሽተኛውን አጠቃላይ ሁኔታ በማጤን የህመሙን ዓይነት የሚለዩበት ስልትም ሌላኛው ባህላዊ የበሽታ መለያ ዘዴ ነው።

ባጠቃላይ ባህላዊ ሃኪሞች በባህላዊ ህክምና ስልት በሽተኛን ለማከም በቀጥታ ወደ መድሃኒት ስብሰባ፣ ዝግጅት፣

ቅመማና አሰጣጥ ሳያመሩ፣ አስቀደመው የበሽታውን ዓይነት የሚለዩባቸው የተለያዩ ባህላዊ የበሽታ መለያ መንገዶች አሏቸው።

## የባህላዊ ዕፅዋት መድሃኒት አሰባሰብ፣ ቅመማና አሰጣጥ

በባህላዊ ህክምና የበሽታው ዓይነት ከተለየ በኋላ ቀጣዩ ተግባር መድሃኒት መሰብሰብ፣ መቀመምና መስጠት ነው። እንደ Sofowora (1982)፣ Alemayehu(1984)፣ መስፍን(2002) እና ተመስገን(2003)ገለጻ፣ ባህላዊ የዕጽዋት መድሃኒት ባለሞያዎች ዕፅዋቱን በአካባቢያቸው በማልማት ወይም ከዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ አካባቢ በመፈለግ ይሰበስባሉ። Young (1970)ና Alemayehu(1984) እንደሚያስረዱት፣ አንድ ባህላዊ ሃኪም ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ግብዓቶችን ለመቀመምና ለመስጠት ዕፅዋቱ የሚበቅሉበትን ቦታ፣ ስያሜ፣ የመሰብሰቢያ ጊዜና ወቅትን ማወቅ፤ የመድሃኒት የመሰብሰቢያ ቁሳቁሶችን መለየትን፤ ዕፅዋት ስለሚሰበሰቡበት ሁኔታና አሰጣጥ የተሻለ ግንዛቤ ሊኖረው እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አሰጣጥን በተመለከተ Alemayehu(1984)፣ መስፍን(2002) እና ተመስገን(2003) ባህላዊ መድሃኒቶች ከተለያዩ ቦታ ተሰብስበው ከተቀመሙ በኋላ ፤ በአፍንጫ እንዲሸተቱ፣ በአፍ እንዲማጉማጉ፣ በሽታው በታየበት የአካል ክፍል ላይ እንዲቀቡ፣ በመርፌ መልክ እንዲሰጡ፣ በአንገት ወይም በክንድ ላይ እንዲጠለጠሉ ሆነው ተዘጋጅተው ለበሽተኛው ወይም ለታካሚው እደሚሰጡ ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ የባህል ሃኪሞች ለባህላዊ መድሃኒት ቅመማ የሚውሉ ዕፅዋትን በተለያዩ መንገዶች ከመኖሪያ አካባቢያቸው፣ ከዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ ቦታ ተሰብስበው እንደ በሽታው ዓነይነትና ባህርይ በተለያየ መልኩ ማለትም፤ የሚጠጡ፣ የሚሸተቱ፣ የሚቀቡና በክታብ መልክ የሚንጠለጠሉ ተደርገው ሊሰጡ ይችላሉ።

## በባህላዊ ዕፅዋት መድሃኒት ዝግጅት ሂደት ባህላዊ መድሃኒት ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባሎችና ዕለታት ተምሳሌታዊ ትርጉም

በባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት በማሰባሰብ፣ በማዘጋጀትና በመቀመም ሂደት የተለያዩ መድሃኒቶችን ለማዘጋጀትና ለመስጠት የተለያዩ ዕለታት ወይም ቀናት ይመረጣሉ። ይህን ሃሳብ በተመለከተ መስፍን(2002) እና ተመስገን(2003) ባህላዊ የመድሃኒት ዕፅዋቱ የሚቆረጡበትና የሚሰበሰቡባቸው ዕለታት ማክሰኞ፣ ረቡዕና ዓርብ ለባህላዊ መድሃኒት መሰብሰቢያ የተመረጡ ዕለታት እንደሆኑ ይገልጻሉ። በተጨማሪም መሪራስ(2006) እና በቀለች(2007) የባህል መድሃኒት ዕፅዋቱን ለመሰብሰብ ቅዳሜና ሐሙስንም መጠቀም እንደሚቻል ይገልጻሉ። እነዚህ ዕለታት ለባህል ዕፅዋት መድሃኒቱ መቁረጫ፣ መቆፈሪያ ወይም መልቀሚያ የተመረጡ ቀናት እንደሆኑና ከእነዚህ ዕለታት ውጭ የሚሰበሰብ የባህል መድሃኒት ዕፅዋት ተገቢውን አገልግሎት እንደማይሰጥ ከብዙዎቹ ምሁራን ገለጻ መረዳት ይቻላል።

የባህል መድሃኒቶች ለተፈለገው ዓይነት ፈውስ ዝግጅት ሲሰበሰቡ የተለያየ ተምሳሌታዊነት ያላቸው የመድሃኒት ዕፅዋት መቆፈሪያ፣ መቁረጫና ማዘጋጃ የሚያገለግሉ ቁሶችም አሉ። ቁሳቁሶቹም፤ የቀንድ ካራ[2](ቢላዋ)፣ የወይራ አንካሴ[3]፣ ውሃ ያልነካ ቅቤ፣ የሰው ደም የነካ ጦር፣ ትክል ድንጋይ፣ ወፍ ያልቀመሰው ዉሃ፣ የጥቅምት ወይም የእስጢፋኖስ ማር[4]፣ የአምሳያ ላም ቅቤ[5] ናቸው። እንዲሁም ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቱን ለማንገስና ፈዋሽ እንዲሆኑ ለማድረግ የዕፅዋት ማንገሻ ጸሎትና ከጸሎቱ ጋርም እምነታዊ ክዋኔና ሥርዓት ገቢርም እንደሚያስፈልጋቸው መስፍን(2002)፣ ተመስገን(2003) እና መሪራስ(2006) ባህላዊ ሃኪሞቹ የሚጠቀሙባቸውን የተለያዩ የ"ዕፅ አንግስ" ጸሎት በማስረጃ ጠቅሰዋል።

በአጠቃላይ ከፍ ሲል ከቀረቡት ሃሳቦች መረዳት የሚቻለው የባህል ሃኪሞች በባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ዝግጅት

---

2 የቀንድ ካራ የሚባለው እጀታው ከቀንድ የተሰራ ቢላዋ ማለት ነው::

3 የወይራ አንካሴ የሚባለው ልክ እንደአንካሴ በመቆፈሪያነት የሚያገለግለው ከወይራ እንጨት የተሰራ አንካሴ መሰል ቁስ ነው::

4 የጥቅምት/ እስጢፋኖስ ማር የሚባለው የጥቅምት ወር በገባ በ17ኛው ቀን የሚቆረጥ ማር ሲሆን ዕለቱ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት እምነት መሰረት በግብረ ሃዋርያት እንደተጠቀሰው ሃዋሪያው እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ የሞተበትና ቃል ኪዳን የተሰጠበት ቀን በመሆኑ ማሩ ለመድሃኒት መቀመሚያና ራሱም እንደመድሃኒት ሆኖ ያገለገላል::

5 የአምሳያ ላም ቅቤ የሚባለው እናትና ልጅ ተመሳሳይ ቀለም ያላቸው ላሞች የሚገኝ ቅቤ ነው::

ወቅት መድሃኒት ለመቀመም የሚሰበስቧቸውን ዕፅዋት ሲሰበስቡ የተለያዩ ተምሳሌታዊ ትርጉምያላቸውን ቀናትና ቁሳቁሶች እንደሚጠቀሙ፤ የተለያዩ የዕፅ ማንገሻ ጸሎቶችን እንደሚጸልዩና የተለያዩ ሥርዓት ክዋኔዎችና ሥርዓት ገቢሮችን እንደሚፈጽሙ ነው።

## የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት፣ የመተላለፊያ መንገድና የማህበረሰቡ አመለካከት

Wondwosen(2006)፣ Young(1970) መስፍን(2002) እና ተመስገን(2003) እና Kokwaro(1976) እንደገለጹት ባህላዊ ሐኪሞች የህክምና ሙያ እውቀታቸውን ማለትም የመድኃኒቱን ዓይነት፣ አሰባሰብ፣ አቀማመምና አሰጣጥ በተመለከተ ከራሳቸው ውጭ ሌላ ሰው በፍጹም እንዲያውቅ አይፈልጉም፤ ስለ ባህላዊ መድሃኒት ጠቀሜታ እና ጉዳትም ለሌላ አካል አይመሰክሩም። መናገር ቢፈልጉም እንኳ በጣም ለሚቀርቡት ቤተሰባቸው ያውም ሊሞቱ በተቃረቡበት ሰዓትና ዕለት በቃል ነው። በዚህ ምክንያት የተላለፈው መረጃ የተቆራረጠና የአድማጩን ክህሎት የሚጠይቅ ይሆናል። በመሆኑም የባህል መድሃኒቱ ዕውቀት ይዛባል፤ አስፈላጊና ጠቃሚ መረጃዎችንም ለመጪው ትውልድ በውል እንዳይተላለፍ ያደርጋል።

እንዲሁም Fekadu(2001) ደግሞ ባህላዊ መድኃኒት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈውም በቃል መሆኑንና በቃል በመሆኑም ብዙ ጊዜ ትክክለኛ መረጃ እንደማይተላለፍና ጠቃሚ የሆኑ የባህላዊ መድሃኒት ዕፆች መረጃ እየጠፋ መሆኑን፤ በተጨማሪም Alemayehu (1984) እና Young(1970) ደግሞ የባላዊ መድሃኒት ጥበብ ሙያ ከጓደኛ በመማር፣ ከቤተሰብ በውርስ (በዘር) በሚገኝ እውቀት፤ ሙያው (እውቀቱ) ያላቸውን ሰዎች ለረጅም ዓመት በማገልገልና አብሮ በመስራት በሚገኝ ጥበብ፣ እውቀቱን በገንዘብ በመግዛት፣ አውደ ጥበብን በመስረቅ የህክምና እውቀቱ እንደሚተላለፍ ይገልጻሉ።

## የጥናቱ ዓላማ

### ዓብይ ዓላማ

ይህ ጥናት በባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ላይ የተደረገ ሲሆን ዋና ዓላማውም የባህላዊ ዕፅዋት መድሃኒት ቅመማ፤ አዘገጃጀት፣ በሽታ የመለያ ዘዴና፣ አሰጣጥን መመርመር ነበር።

### ንዑሳን ዓላማዎች

ጥናቱ ከላይ በተጠቀሰው ዓብይ ዓላማ ላይ በመመርኮዝም የሚከተሉት ንዑሳን ዓላማዎች ተግባራዊ አድርጓል።

- በባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ዝግጅት ሂደት ለመድሃኒትነት የሚያገለግለውን የዕጽዋት ክፍልና አዘገጃጀት መግለጽ፤
- በባህላዊ መድሃኒት ዝግጅት ሂደት የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎችን፣ ስርዓት ገቢሮችንና የዕፅዋት መሰብሰቢያ ዕለታት ተምሳሌታዊ ትርጉም ማሳየት፤
- በባህላዊ መድሃኒት ዝግጅት የባህላዊ ሃኪሞቹን ባህላዊ የበሽታ መለያ ዘዴ መግለጽ፤
- በባህላዊ መድሃኒት ዝግጅት ሂደት የባህላዊ መድሃኒት አቀማመምና አሰጣጥን ማሳየት፤
- የባህላዊ መድሃኒት ጥበብ ተስተላልፎ፣ ምስጢራዊነትና የማህበረሰቡን አመለካከት መግለጽ፤

## የአጠናን ዘዴ

### የጥናቱ ንድፍ(Design )

ይህ ጥናት በባህርይው ዓይነታዊ መረጃዎችን የሚጠቀም በመሆኑ ገላጭ የምርምር ንድፍን በመከተል ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅሟል። በዚህ ዘዴ ላይ በመመርኮዝም የጥናቱ ተሳታፊዎችን አመራረጥ፣ ለጥናቱ የሚያስፈልገው መረጃ የተሰበሰበበትን መንገድና የመረጃ የተተነተነበትን ዘዴ ቀጥለን እንመለከታለን።

### የጥናቱ ቦታና የተሳታፊዎች አመራረጥ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የባህል ሃኪሞችን ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አቀማመም አዘገጃጀትና አሰጣጥን መመርመር ነው። ይህን ዓላማ ለማሳካት የተመረጠው የጥናት ቦታም ጎንደር ከተማና አካባቢው ነው። በዚህ የጥናት ክልል

ውስጥ በስድስት አብያተ ክርስትያናት ውስጥ ስድስት የባህል ሃኪሞችና ከጎንደር ከተማ ውጭ ደግሞ በሁለት አብያተ ክርስትያናት ውስጥ የሚገኙ ሁለት የባህል ሀኪሞች በዒላማዊ የንሞና ዘዴ ተመርጠዋል። ለጥናቱ የተመረጡት አብያተ ክርስትያናትና የባህል ሀኪሞች የተለያዩ የአብነት ትምህርቶችን ለመከታተል መኖሪያቸውን በዚያ በማድረጋቸውና አካባቢው ለዚህ ጥናት ዋና ዓላማ መሳካት አስፈላጊ መረጃ ለማግኘት ያስችላል ተብሎ ስለታመነበትም ነው።

### የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለዚህ ጥናት የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በግብዓትነት ለማሰባሰብ ይቻል ዘንድ ጥናቱ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን እንደአስፈላጊነታቸው ተጠቅሟል። ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን በቃለ መጠይቅና በምልከታ ተሰብስበዋል። ተመስገን(2003፣11)፣ Goldstain(1964፣77-104) እና Kotak(1991፣23) እንደሚሉት እነዚህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከመስክ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመራጭ ዘዴዎች ናቸው።

በጥናቱ ሂደት ጥቅም ላይ የዋለው ተሳትፏዊ ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ተሣትፏዊ ምልከታ ጥቅም ላይ ውሏል። ምክንያቱም ተሳትፏዊ ምልከታ ከሁሉም መረጃ አቀባዮች ጋር በመሆን የባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቶች የሚገኙበት ቦታ ድረስ በመሄድ ከዕፅዋትና ከዕፅዋት ተዋፅኦዎች ናሙና አሰባሰብንና በአሰባሰብ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችና የመድሃኒት ዕፅዋቱ መሰብሰቢያ ዕለታት፣ ባህላዊ ሃኪሞቹ ዕፅዋቱን ሲሰበስቡ የሚከውኑትን ስርዓተ ክዋኔና የሚጸልዩትን የዕፅዋት ማንገሻ ጸሎት፣ የትኛውን የዕፆቹ አካል ለመድሃኒትነት እንደሚወስዱ መመልከት አስችሏልና። በተጨማሪም ተሳትፏዊ ምልከታ ዕፅዋቶቹ ለየትኛው በሽታ እንደሚውሉ እና እንዴት እንደሚቀመሙ፣ ለመቀመሚያ የሚያስፈልጉ ሌሎች ግብዓቶችና የባህላዊ መድሃኒት ተጠቃሚ ህመምተኞች ስሜት ምን እንደሚመስል ለመቃኘት ጥቅም ላይ ውሏል።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በተጨማሪ መደበኛና ኢ-መደበኛ ቃለመጠይቆች ጥቅም ላይ ውለዋል። ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን እንደሚገልፁት እነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተወሰነ ማኅበረሰብን ባህልና ልማድ ለማጥናት የሚጠቅሙ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው። በመሆኑም በጥናቱ መደበኛና ኢ-መደበኛ ቃለመጠይቆች አማካኝነት ማህበረሰቡ ለባህላዊ መድሃኒት ያለው አመለካከት ምን እንደሚመስል፣ የባህላዊ መድሃኒት ምስጢራዊነትና ተስተላልፎን የሚመለከቱ መረጃዎች ከመስክ ተሰብስበዋል። ከእነዚህ የቃለመጠይቅ ዓይነቶች ውስጥ ውስን ቃለ መጠይቅ፣ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅና ነፃ ቃለመጠይቅ በማድረግና እነሱንም እንደአመቺነታቸው እያፈራረቁ በመጠቀም መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተሞክሯል። ያለው(2009፣185) ገለጸ፤ ነፃ ቃለ መጠይቅ ነጻነትን ለመላሹም ለተመራማሪውም ይሰጣል፣ እንዳሉት በጥናቱ ሂደት ነጻ ቃለመጠይቅ መረጃ አቀባዮቹ ሳይፈሩ፣ ሳይሳቀቁ፣ ሳይጨነቁ ስለ ባህላዊ መድሃኒት ያላቸውን አመለካከት፣ ግንዛቤና እውቀት ለመቃኘት ያስቻለ ከመሆኑም በተጨማሪ በባህላዊ መድሃኒት ዙሪያ በርካታ መረጃዎችንም ለመሰብሰብ አግዟል።

በአጠቃላይ በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችና ዘዴዎች የተገኙ መረጃዎች እንደአመቺነታቸው በፎቶግራፍ፣ በቴፕና በማስታወሻ ተቀርጸው፣ ተቀድተው በመሰነድ ለጥናቱ በግብዓትነት አገልግለዋል።

### የመረጃ መተንተኛ ዘዴ

ከላይ በጥናቱ ዘዴ ለመጠቆም እንደተሞከረው ጥናቱ በዓይነታዊ የምርምር ዘዴተከናውኗል። ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ለትንታኔ ከመቅረባቸው በፊት መልሶች በትክክል ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ተጣርቶ፣ ለትንተና በሚመች መልኩ በማደራጀትና የማጣራት ስራ በመስራት በገላጭና በይዘት ትንተና መረጃ መተንተኛ ሥልቶችን በመጠቀም ለመተንተን ተሞክሯል።

### የመረጃ ትንተና

ለባህላዊ መድኃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶች፣ ዓይነት፣ አገልግሎት፣ አሰባሰብና አዘገጃጀት


| | የዕፅዋቱ ስም | | | የዕፅዋቱ መድሃኒትነት | አዘገጃጀት |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማርኛ | ግዕዝ | ሳይንሳዊ ስም | | |
| 1 | መቅመቆ | ዕፀ ብርሃን | Rumex abyssinicus | ሀ*. ለቁርጥማት<br>ለ. ሰገራ ለከለከለው/ ለሚያስምጠው<br>ሐ. ለእከክ<br>መ. ለሳልለደም ብዛት--<br>ሠ. ለደም ጥራት | ሀ. ከሰሊጥና ከኑግ ቅባት ጋር ቀቅለህ በባዶ ሆድ መጠጣት<br>ለ. ከወተት ጋር አፍልቶ ማጠጣት<br>ሐ. አድርቆ፣ ፈጭቶ በቅቤ ለውሶ መቀባትና እሳት ማሞቅ<br>መ. ከጦስኝና ከእንጭብር ጋር በቅቤ አንጥሮ ማጠጣት<br>ሠ. እንደ ሻሂ ቅጠል በመጠቀም አዘውትሮ መጠጣት |
| 2 | የአይጥ ሃረግ | ዕፀ ኢየሱስ | Cissampelos Mucronata | ሀ. ሱስን ለመተው<br>ለ. ለትምህርት | ሀ. ሱስ የተያዘበትን ነገርና የአይጥ ሃረጉን ፍሬ ባንድ ላይ አድርጎ መስጠት<br>ለ. ስሩን ቆፍሮ የጠገራ ብር የሚመስል ነገር ሲያገኙ ከእስጢፋኖስ ማር ጋር መብላት |
| 3 | ጥንጁት | - | Otestegia | ሀ. ለሳል<br>ለ. ለደረቅ የሆድ ቁርጠት<br>ሐ. ደም ብዛትን ለማከም | ሀ. አበባውን አጠራቅሞ እንደ ሲጋራ በወረቀት ጠቅልሎ ወይም በጋያ መሳብና ማጨስ፤ ከዚያም አንት መጠጣት<br>ለ. ቀንበጡን ቆርጦ ማላመጥ<br>ሐ. ቅጠሉን አድርቆና ፈጭቶ ከቡና ቅጠል ጋር አፍልቶ በማር ማጠጣት |
| 4 | ወርቅ በሜዳ | ዕፀ ወርቄ | Coccinia Sp. | ሀ. ጊንጥ ለነደፈው<br>ለ. እባብ ለነደፈው<br>ሐ. ለጥርስ ህመም<br>መ. ጉሮሮው ላበጠ | ሀ. ስሩን በጥርስ አላምጦ የተነደፈው የሰውነት ክፍል ላይ ማሰር<br>ለ.ስሩን በጥርስ አላምጦ የተነደፈው የሰውነት ክፍል ላይ ማሰር<br>ሐ. ስሩን ወይም አበባውን አላምጦ በታመመው ጥርስ መያዝ<br>መ. ከዕጸ መናሂ ጋር ወቅጦ በአምሳያ ላም ቅቤ ቁስሉን መቀባት |
| 5 | እንዶድ | - | Pytolacca Do-decandra | ሀ. ለእብድ ውሻ በሽታ<br>ለ. ለቁርባ<br>ሐ. ለአባ ሰንጋ | ሀ. ከስሩ በእጅ ጣት አንጓ አንድ ለክቶ በመቁረጥና በመፍጨት በውሃ ዘፍዝፎ ለሰባት ቀን ማጠጣት<br>ለ. ሥሩን ወይም ቀንበጡን ወቅጦ ግማሽ ማንኪያ ማጠጣት ነው፡፡መመለሻው ቡና መስጠት<br>ሐ. ቀንበጡን በትንሹ መስጠት፡፡ ልብን ስለሚያደክም ተልባ በጥብጦ መስጠት ነው፡፡ |
| 6 | ወይን | ዕፀ ወይን | Vitis Vi-nifera | ሀ. ለምግብና ለቤ/ ክርስቲያን<br>ለ. ለትውከትና ለቁርጠት<br>ሐ. ለወገብ ህመም | ሀ. የወይን ፍሬውን ቢፈልጉ ርጥቡን ፍሬ ቢፈልጉ የደረቀውን ፍሬ/ ዘቢብ ቢመገቡት ለብዙ ነገር ይሆናል፡፡<br>ለ.ደረቁን የዘቢብ ፍሬ በባዶ ሆድ መብላት<br>ሐ. ቅጠሉን ወቅጦ በውሃጨምቆ ማጠጣት |
| 7 | ሳማ | ዕፀ ሌላም/ አስማ | Urtica si-mensis | ሀ. ለጨጓራ<br>ለ. ሴት ልጅ በሰላም እንድትወልድ<br>ሐ. ለምግብ<br>መ. ደም ለሚያስታውከው | ሀ. ቅጠሉን እንደጎመን ቀቅሎ አዘውትሮ መመገብ<br>ለ. የሳማ ስር ወቅጦና በተልባ አሹቶ ማጠጣት<br>ሐ. ቅጠሉን እንደ ሀበሻ ጎመን ቀቅሎና ሰርቶ መመገብ<br>መ. ቅጠሉን ወቅጦና ጨምቆ በባዶ ሆድ ማጠጣት |

| | የዕፅዋቱ ስም | | | የዕፅዋቱ መድሃኒትነት | አዘገጃጀት |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማርኛ | ግዕዝ | ሳይንሳዊ ስም | | |
| 8 | ቀረጥ | - | Osyris sp | ሀ. በቆዳ ላይ ለሚወጣ ኪንታሮት<br>ለ. ቁስል ለማድረቅ | ሀ. በቀላው የቀረጥ ፍሬ ደጋግሞ ማሸት<br>ለ. የቀረጥ ቅጠል ከወርጠብና ከክትክታ ቅጠል ጋር ወቅጦ በቁስሉ ላይ መደምደም |
| 9 | ኮሶ | ዕፀ አባብ | Hagenia Abyssi-nica | ሀ. ለኮሶ ትላትል<br>ለ. ለደም ብዛት | ሀ. ፍውን በተወቀጠ ኑግና በማር ለውሶና በጥብጦ ማጠጣት<br>ለ. የኮሶውን ፍና አበባ በመውቀጥ በማር ማጠጣት |
| 10 | እሬት | ዕፀ እጉሰታር/ መሪር/ረሃ/ሪሃ | Aloe abyssi-nical | ሀ. ለስኳርና ለልብ ህመም<br>ለ. ለማድያት<br>ሐ. ለቁርጥማት | ሀ. የእሬቱን የውስጥ ስጋ ከምድር እንቧይ ፍሬ ጋር ወቅጦ መስጠት<br>ለ. የእንዳውላ አበባ ሰብስቦ በመውቀጥ ማድያቱን መቀባት<br>ሐ. ስሩን ወቅጦ አልሞ ለብዙ ቀን በጥቅምት ማር መስጠት |
| 11 | ዳማ ከሴ/ ከሴ | ዕፀ ቀኖና | Ocimum Tamifo-lium | ሀ. ለምች | ሀ.ቅጠሉን አጥቦና ቀቅሎ ዉሃውን በትኩሱ መታጠንና እንደ ሻሂ መጠጣት<br>ለ.ቅጠሉን ጨምቆ በትንሹ መጠጣትና አፍንና አፍንጫን አሸት አሸት ማድረግ |
| 12 | ጽጌረዳ አበባ | ዕፀ መርሳኒ | Vitis Vinfera | ሀ. ለሽቶ ዝግጅት<br>ለ. ለትምህርት<br>ሐ. ጆሮው ላበጠ | ሀ. አበባውን በብዛት ለቅሞ ከሌሎች አበባ ዘሮች ጋር መደቆስና መጭመቅ<br>ለ. አበባውን በብዛት ለቅሞ ከሌሎች አበባዎች ጋር ወቅጦ በእስጢፋኖስ ማር መጠጣት<br>ሐ. አበባውንና ቅጠሉን ባንድ ላይ ቀቅሎ ጥላዩን በጆሮው ማስገባት |
| 13 | ወርጠብ | ዕፀ ናህም | Plantain | ሀ. ለአዲስ ቁስል<br>ለ. ለኩላሊት/ /ለጣፊያ/ | ሀ. ቅጠሉን ጨምቆ አዲሱን ቁስል ላይ መደምደም<br>ለ. የወርጠብ ቅጠሉን አድርቆ በመፍጨት አንድ ማንኪያ ዱቄት በአንድ ማንኪያ ንጹህ ማር ጋር በ ሞቀ ውሃ ማገናኘትና ህመሙ እስኪሻል ድረስ መጠጣት፡፡ |
| 14 | ጠለንጅ | ዕፀ ዌና | | ሀ. ለቋቁቻ | ሀ.ገላን ታጥቦ እርጥቡን ቅጠል ደቁሶ ቋቁቻን ደጋግሞ በተደቀሰው ቅጠል ደጋግሞ ማሸትና መቀባ |
| 15 | ጨጎጎት/ የካህን ቁም | ዕፀ ፍቅር | Cyathula polyceph-ala | ሀ. ለራስ ምታት<br>ለ. ሌሎች በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት | ሀ. ቅጠሉን ከዳማሴ ቅጠል ጋር ወቅጦ በአፍንጫ መሳብ |

| | የዕፅዋቱ ስም | | | የዕፅዋቱ መድሃኒትነት | አዘገጃጀት |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማርኛ | ግዕዝ | ሳይንሳዊ ስም | | |
| 16 | ነጭና ቀዩ አዞ አረግ | - | Clausena anisate | ሀ. ለቁስል፣ ለሻህኝ<br>ለ. ለአህያ ኪንታሮት፣ ለጎርምጥና ለቆላ ቁስል<br>ሐ. አልመግል ላለ እበጥ<br>መ. ለኪንታሮት<br>ሠ. ለጥርስ ህመም | ሀ. በሎሚ ውሃ ቁስሉን አጥቦ የቁስሉን ዙሪያየማር ወለላ ቀብቶ በቁስሉ ላይ የአዞ ሀረግ ቅጠልወቅጦና አድርቆ መደምደም፣ በበላዩ የሥንዴ ሊጥ ደፍድፎ በሻሽ ለሶስት ቀን ማሰር እና በሶስተኛው ቀን መፍታት ነው:: ሁሉ ካልወጣ መድገም ሲድን የድግጣ ቅጠል አሽቶ መቀባት<br>ለ. ሰናፍጭ፣ እንክርዳድ ተወቅጦ ከአዞ ሃረግ ቅጠል ጋር ለውሶ በቁስሉ ላይ መደምደም<br>ሐ. ቅጠሉን ወቅጦ በሚያመው ላይ መደምደም፤ ወዲያው ይፈነዳል::<br>መ. ቅጠሉን ወቅጦ በቅጭብ ወተት በመለወስ ቁስሉ ላይ ማር አድርጎ መቀባት<br>ሠ. ቅጠሉን ወቅጦ ከሚያመው ላይ ደምድሞ ጥቂት ደቂቃ ማቆየት |
| 17 | ለንቋጣ | ዕፀ ድህነት | Grewia Fer-rugineae | ሀ. ለጨነኛ የሆድ እቃ<br>ለ.ለፎረፎርና ለቅማል<br>ሐ. ሰገራ ለከለከለው | ሀ. ልጡን አድርቆ በመውቀጥ ከቅመም ጋር ጨምሮ ምግብ ሰርቶ መብላት<br>ለ. ቅርፍቱንና ፍውን ባድ ላይ አድርጎ ደቁሶ መቀባት<br>ሐ. ልጡን ከእስላል ጋር ማጠጣት |
| 18 | ስረ ብዙ | ዕፀ ሠርዌ | Thalictrum Rhynchope-talum | ሀ. ለቆላ ቁስል<br>ለ. ለምች<br>ሐ. ለደም ብዛት | ሀ. ቅጠሉን አድርቆ ከጨው ጋር በመውቀጥ በቁስሉ ላይ መደምደም<br>ለ. ስሩን ቀቅሎ በውሃው መታጠን<br>ሐ. ስሩን ወቅጦ በማር ማብላት ነው:: |
| 19 | አውጥ | - | Solanum Nigrum | ሀ. ለደም ብዛት<br>ለ. ወስፋት ለያዘው<br>ሐ. ለእንጀራ ማስቀመጫ<br>መ. ለቂጥኝ<br>ሠ. ለነቀርሳ | ሀ. ቅጠሉንና ስሩን ወቅጦና አፍልቶ ማጠጣት ወይም በማር ለውሶ ለውሶ ሳይበዛ ማብላት<br>ለ. ቅጠሉን ቀቅሎ በገንፎ መብላትና አጓት ማጠጣት<br>ሐ. ቅጠሉን ቆርጦ ጉዝጓዝ ማድረግ እንጀራው በጣም እንዲለሰልስና እንዲያምር ያደርጋል<br>መ. ከስሩ በተጨማሪ ዘርጭ እንቧይና የአንፋር ስራቸውን ወቅጦ መቀቀልና ማጠጣት<br>ሠ.ከስሩ በተጨማሪ ዘርጭ እንቧይና የአንፋር ስራቸውን ወቅጦ በነቀርሳው ላይ ማሰርና ከዚያም የዝግጣ ቅጠል ወቅጦ መደምደም |
| 20 | እንዳውላ | - | Kalanchoe Densiflora | ሀ. ለችፌ<br>ለ. ለማድያት<br>ሐ. ለእባጭ<br>መ. ለጥርስ ህመም | ሀ. ስሩን መውቀጥና ውሃ ባልነካ ቅቤ ለውሶ ከቁስሉ ላይ መደምደም ከተቻለ እሳት ማሞቅ<br>ለ. የእንዳውላ አበባን ሰብስቦና ወቅጦ ፊትን/ ማድያቱን መቀባት<br>ሐ. ሥሩን በሚገባ መውቀጥና ማድረቅ፤ እበጡን በአዲስ ምላጭ መብጣትና በተበጣው ክፍል ላይ መድሃኒቱን መደምደም<br>መ. ሥሩን በማላመጥ ከሚያመው ላይ ነክሶ መያዝ ወይም ደቁሶ ከታመመው ጥርስ ላይ መደምደም |

| | የዕፅዋቱ ስም | | | የዕፅዋቱ መድሃኒትነት | አዘገጃጀት |
|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | አማርኛ | ግዕዝ | ሳይንሳዊ ስም | | |
| 21 | የሰይጣን መርፌ | - | Bidens Pilosa | ሀ. ለነስር<br>ለ. የሚፈስ ደምን ለማቆም<br>ሐ. ደም አልቆም ላላት ሴት<br>መ. እባብ ለነደፈው | ሀ. ስሩን ወቅጦ በጥቅምት ማር/ ከተገኘ/ ማብላት ወይም በአፍንጫ መማግ<br>ለ. ቅጠሉን አሽቶ የሚፈሰው ቦታ ላይ ማድረግ<br>ሐ. ቅጠሉን ቀቅሎ ማጠጣት<br>መ. ስሩን ወቅጦ ጨምቆ መጠጣት |
| 22 | አቱች | ዕፀ መንግስት | Verbena Officialis | ሀ. ለጉሮሮ ህመም<br>ለ.ምላሱን ለታመመ<br>ሐ. ለእንጥል ህመም | ሀ. ቅጠሉን በውሃ ቀቅሎ በትኩሱ ውሃ መጉመጥመጥ ቅጠሉን አንገት ላይ መደፍደፍ<br>ለ. ቅጠሉን ቀቅሎ በትኩሱ ውሃ ደጋግሞ መጉመጥመጥ<br>ሐ. ቅጠሉን ጨምቆ በትንሹ መጠጣት/ ህጻናት ከሆኑ እናትዬዋ አላምጣ አፉ ላይ ጭማቂውን ጠብታድርግ |
| 23 | ዋጅነስ | ዕፀ ጌኖ | Brucea antidisenterica | ሀ. ለጭርት<br>ለ. ለችፌ<br>ሐ. ለእብድ ውሻ በሽታ<br>መ. ለአስም<br>ሠ. ጀርባው ለወጣ | ሀ. ቅጠሉን ከአዞ ሀረግ ጋር አድርጎ በመውቀጥ እና የቁሱሉን ዳር አስቀድሞ ማር መቀባትና በላዩ ላይ ደምድሞ በሻሽ መሸፈን፡፡<br>ለ. ቅጠሉን ከአዞ ሀረግ ጋር አድርጎ በመውቀጥ እና የቁሱሉን ዳር አስቀድሞ ማር መቀባትና በላዩ ላይ ደምድሞ በሻሽ መሸፈን፡፡<br>ሐ. ስሩን ወቅጦ በጥቅምት ማር ለውሶ መዋጥ<br>መ. ፍሬውን ወቅጦ በጥቅምት ማር ማዋጥ፡፡ በጣም ያሥታውካል ግን ፍቱን ነው፡፡<br>ሠ. ቅጠሉን ከነጭ ሽንኩርት ጋር ወቅጦ በአምሳያ ላም ቅቤ መቀባት፣ ይቆስላል ግን ይድናል |
| 24 | ቀጠጢና | ዕፀ እስራኤል/ ደብተራ | Verbascum sinaiticum | ሀ. ለጨጓራ<br>ለ. የወር አበባ ለሚበዛባት ሴት<br>ሐ. አልድን ላለ ቁስል<br>መ. ለራስ ምታት በሽታ<br>ሠ. ለችፌ | ሀ. ፍውንና ስሩን ወቅጦ በተልባ ጭልቃ አድርጎ ማጠጣት<br>ለ. ከጠለንጅ ስር ጋር ወቅጦ ሰባት ቀን ያህል በጥቅምት ማር ማዋጥ፡፡<br>ሐ. ቅጠሉን ከወር ጠብ ቅጠል ጋር አልሞ መውቀጥና ማድረቅ፣ ከዚያም በቁስሉ ላይ ማድረግ<br>መ. የቀጠጥና እና የአደይ አበባ ባድላይ መውቀጥ በአፍንጫ እዲምግ ማድረግ<br>ሠ ቅጠሉንና የምድር እንቧይ ስር ጋር ወቅጦ በቁስሉ ላይ መደምደም |
| 25 | ጤና አዳም | - | | ሀ. ዓይኑ ለቀላና ለታመመ<br>ለ. ለሳል<br>ሐ. የተመረዘን መብል ለበላ<br>መ. በእባብ ለተነደፈ<br>ሠ. ለሁሉም | ሀ. ቅጠሉን አጥቦ መቀቀልና በውሃው ማጠብ<br>ለ. ከእንስላል ጋር እያፈሉ መጠጣት<br>ሐ. ቅጠሉን ጨምቆ ቶሎ ማጠጣት<br>መ. አንድ እፍኝ የጤና አዳም ቅጠልና ፍሬ ደቁሶ በብርጭቆ ጨምቆ በሁለት ማንኪያ ንጹህ ማር ጋር በጥብጦ ማጠጣት<br>ሠ. ከሚበሉት ከሚጠጡት ጋር አብረው ቢወስዱት ለጤንነት በጣም ጠቃሚ ነው |

*** በዚህ ለባህላዊ መድሃኒት ቅመማ የሚውሉ ግብዓቶችና አገልግሎታቸውን ለማሳየት በቀረበው ሰንጠረዥ ውስጥ የዕፅዋቱ መድሃኒትነት በሚለው ስር የተጠቀሱት ፊደላት፣ ምሳሌ በ"ሀ" ለተገለጸው የበሽታ ዓይነት አዘገጃጀት በሚለው ስር የሚገኘው "ሀ" ለዚሁ በሽታ መድሃኒቱ እንዴት እንደሚዘጋጅ የተገለጸ መሆኑን ልብ ይሏል ለባህላዊ መድሃኒት ቅመማ የሚውሉ ዕፅዋት አሰባሰብ**



10. እሬት(እፀ እጉስታር)



23. ዕፀ ጌኖ (ሞዲንስ)



11. ደማካሴ (ዕፀ ቀኖና)



22. ዕፀ መንግስት (አቹች)



13. ወርጠብ (ዕፀ ናሆም)



24. ቀጠጢና (እፀ እስራኤል)



19. ዕፀ አውጥ



25. ጤና አዳም

ከዚህ በላይ ለማየት እንደተሞከረው ከተለያዩ የዕፅዋት ዓይነቶች የተለያዩ ባህላዊ መድሃኒቶችን ማዘጋጀት እንደሚቻል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ደግሞ ተጠኚ የባህል ሐኪሞች ለባህል መድሃኒት የሚያገለግሉ ዕፅዋትን የሚሰበስቡባቸውን ቦታዎችና ወቅቶችን እንመለከታለን፡፡

በዚህ ጥናት የተሳተፉ የባህል ሃኪሞች ለባህላዊ መድሃኒት የሚጠቀሙባቸውን የተወሰኑ ዕፅዋቶችን በተለያዩ አልባሌ ቦታዎች በመትከል፤ በተለያየ የአየር ንብረት ባላቸው የዕፅዋቱ ተፈጥሯዊ መገኛ ቦታዎች በማፈላለግና ከሌሎች የዕፅዋት መድሃኒት አዋቂዎች በመግዛትና ሰጥቶ በመቀበል ወይም በለውጥ እንደሚያገኙና እንደሚጠቀሙ መሪጌታ ለይኩን፣ መሪጌታ ስቡህ፣ መምህር ዮሴፍ፣ ቄስ ለማ፣ መሪጌታ ህላዌ፣ መሪጌታ ስሙር ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ /2006ዓ.ም)።

የባህል ሃኪሞች ለባህላዊ መድሃኒት የሚጠቀሙባቸውን ዕፅዋት ከሚሰበሰቡበት ቦታ በተጨማሪ የዕፅዋቱን መሰብሰቢያ ወቅት በተመለከተ የባህል ሃኪሞቹ የተለያዩ ወቅቶችን ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ የባህል ሃኪሞች እንደገለጹት ባህላዊ መድሃኒቶችን ከሰኔ እስከ ህዳር ባሉት ወራት ውስጥ ይሰበስባሉ፡፡ በዚህ ወቅት የሚሰበስቡበት ምክንያትም ሰኔ ላይ ዝናብ ሲዘንብ የሚበቅሉና ቶሎ የሚጠፉ የዕፅዋት ዓይነቶች በመኖራቸው እንደሆነ መሪጌታ ህላዌ፣ መሪጌታ ስቡህና ቄስ ለማ ያስረዳሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ/2006 ዓ.ም)፡፡

መሪጌታ ለይኩን፣ መሪጌታ ስቡህ እና መሪጌታ ስሙር ደግሞ በበኩላቸው የመድሃኒት ዕፅዋቱን የሚሰበስቡት ከጳጉሜ እስከ ህዳር መጀመሪያ ባለው ጊዜ ውስጥ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ምክንያታቸውን ሲገልጹም "ወቅቱ የዕፅዋቱ ስር፣ ቅጠል፣ ቅርንጫፍ ልምላሜ ያለውና አበባም የሚያብብበት ወቅት በመሆኑ ነው በማለት ያብራራሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ /2006ዓ.ም)፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሃሳብ የምንረዳው የባህል ሃኪሞቹ ባህላዊ መድሃኒት ዕፅዋቱን ከተለያዩ ቦታዎችና የአየር ንብረት ባላቸው ቦታዎች እንደሚሰበስቡ ነው፡፡ ምክንያቱም የዕፅዋቱ መገኛም እንደበሽታውና እንደባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቱ ዓይነት የሚለያይ በመሆኑ ነው፡፡ በርግጥ የባህል ሀኪሞቹ ሁሉንም የመድሃኒት ዓይነት በአንድ ጊዜ ቆርጠው ብቻ አይጠቀሙም፡፡ በጥናቱ የተሳተፉ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች መሪጌታ ህላዌ፣ መሪጌታ ስሙርና መሪጌታ ይባቤ እንደገለጹት ዕፅዋቱ አንድም በርጥብነቱ ለመድሃኒትነት ሊያገለግል፤ አንድም በርጥብነቱ ቆርጦ በማድረቅ ራሱን ችሎ ወይም ከሌሎች ዕፅዋት ጋር ተደባልቀው ጥቅም ላይ ስለሚውሉ በእነዚህ ወራት ውስጥ ዕፅዋቱን በመሰብሰብና አድርቆ በማዘጋጀት ዓመቱን ሙሉ በባህላዊ መድሃኒትነት መጠቀም እንደሚቻል ይገልጻሉ (ቃለመጠይቅ፣ ሐምሌ/ 2006ዓ.ም)፡፡

እርግጥ ነው በእነዚህ ወቅቶች የሚሰበሰቡ ዕፅዋት ቅጠላቸው፣ ስራቸው፣ አበባቸው፣ ፍሬያቸውና ቅርፊታቸው ከነሙሉ ተፈጥራዊ መዓዛቸው የሚገኙበት ወቅት በመሆኑ ወቅቱ አመች መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በጥናቱ ሂደትም አጥኚው ለማረጋገጥ እንደሞከረውና በተለይ ይህ ጥናት በዩኒቨርሲቲው በጀት የተበጀተለት ህዳር ማለቂያ አካባቢ በመሆኑ ምክንያት የባህል ሃኪሞቹ ሁሉንም የባህል መድሃኒት አስቀድመው በማሰባሰባቸው ጥናቱ ምልከታውን ለማድረግ የግድ መጭውን ሰኔ መጠበቅ ግድ ሆኖበት ነበር፡፡ በዚህም የባህላዊ መድሃኒት ባለሙያዎች ዕፅዋቱን የሚሰበስቡበት ወቅት ከላይ እንደተገለጸው ከሰኔ እስከ ህዳር ያለው ጊዜ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡
ለባህላዊ መድኃኒት መሰብሰቢያና መቀመሚያ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች እና ቀናት ትዕምርታዊነት

መሪጌታ ስሙር "ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ዕፅዋቶችን በመቁረጥ፣ በመቆፈር ሂደት የዕፅ ዓይነቱን መለየት፣ ዕፁ በየትኛው አካባቢ እንደሚገኝና በየትኛው ጊዜና ወቅት እንደሚቆረጥ፣ እንዴት እንደሚዘጋጅ ማወቅን ይጠይቃል፡፡ ለምሳሌ፣ አንዳንድ የባህል መድሃኒት ዕፅዋት ማክሰኞ የሚቆረጡ ረቡዕ የማይቆረጡ አሉ፣ ዓርብ የሚቆረጡ ሐሙስ የማይቆረጡ አሉ፡፡ እህል ሳይቀመስ በባዶ ሆድ የሚቆረጡ ወይም የሚቆፈሩ ዕፅዋት አሉ፡፡ ዝም ተብሎ አይቆረጥም፤" በማለት ያስረዳሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ /2006ዓ.ም)።
የባህል ሃኪሞቹ የባላህዊ መድሃኒት ዕፅዋትን ለመቁረጥ፣ ለመቆፈር፣ ለመቀመምና ለመስጠት ባህላዊና እምነታዊ ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ቁሳቁሶች እና ቀናትን ይጠቀማሉ፡፡ በባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አሰባሰብና ዝግጅት ሂደት የቀንድ ካራ/ቢላዋ፣ የወይራ አንካሴ፣ ወፍ ያልቀመሰው ውሃ፣ ትክል ድንጋይ፤ የአምሳያ ላም ቅቤ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን፣ ከቀናት ደግሞ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ዓርብና ቅዳሜ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቱ የሚቆረጥባቸውና የሚሰበሰብባቸው ቀናት ናቸው፡፡

እነዚህ ቁሳቁሶች እና ቀናት ለዕፅዋት መድሃኒት መቁረጫ፣ መቆፈሪያና ማዘጋጃነት የተመረጡበት ምክንያት ከባህል መድሃኒት ጋር የተያያዘ የራሳቸው የሆነ ትልቅ ዋጋ እንዳላቸው የባህል ሃኪሞቹ ይገልጻሉ። ለምሳሌ፣ ከወይራ እንጨት የተሰራ የወይራ አንካሴ ዕፅዋቱን ለመቆፈር የሚያገለግል ቁሳዊ ባህል ነው። ወይራ እንጨት ብዙ ጊዜ

በመጽሐፍ ቅዱስ ትልቅ ቦታ ያለው፣ ለቤተክርስቲያን ጣሪያና ግድግዳ መሥሪያ እና ለቅብዐ ቅዱስ ማዘጋጃ የሚያገለግል ተመራጭ ዕፅ ነው። በመሆኑም በወይራ አንካሴ የሚቆረጥና የሚቆፈር ዕፅ መድሃኒትነቱ ፍቱን ነው፤ ፈውስም ያስገኛል። የወይራ አንካሴ እንደ ባህላዊ መድሃኒቱ ዓይነት አንድም ወይራ እንጨቱ ብቻ እንደ አንካሴ ሆኖ፣ አንድም በወይራ እንጨት ጫፍ ላይ የሰው ደም የነካ ነባር ጦር ሊገጠምበት ይችላል። የነባሩ ጦር ፋይዳ የሰው ደም መንካቱ የባህላዊ መድሃኒት ዕፅዋት በባህርያቸው የደም ግብር የሚፈልጉ በመሆናቸው ነው። ለምሳሌ ዕፀ ጊሜ ወይም ጊሜ ሃረግ የሚባለው ዕፅ ሲቆረጥ ወይም ሲሰበሰብ በባህርይው የባህል መድሃኒት ሃኪሙ እጁ ላይ ወይም ሌላ የሰውነት አካሉ ላይ በስለት በመቁረጥ ወይም በመብጣት በራሱ ደም ዕፁን አስነክቶ መቁረጥ ያስፈልገዋል። ይህን የሚያደርግበት ምክንያትም ከዕፁ ጋር ያሉት ጠባቂ መናፍስት ባህል ሃኪሙን እንዲዋረሱትና መድሃኒቱን መጠቀም እንዲችል ወይም እንዲሰራለት ነው። ደም በነካው የቀንድ ካራም ዕፅዋቱ ሲቆረጡ ዕፆቹ ለምንፈልገው ሁሉ ይሰራሉ፤ ይሰምራሉ። ዝም ብለን ብንቆርጠው ግን አይሰራም፤ በማለት ይገልጻሉ(ቃለ መጠይቅ፣ መሪጌታ ሕላዌ፣ መሪጌታ ስሙር ፣ መሪጌታ ኤልያስ፤ ሰኔ /2006 ዓ.ም)።

ሌላው በባህላዊ መድሃኒት ዝግጅት ሂደት ለባህላዊ መድሃኒት የሚያገለግሉ መቁረጫና መቆፈሪያ ከሚያገለግሉ ቁሶች ውስጥ የቀንድ ካራ ወይም ቢለዋ አንዱ ነው፡፡ አሰራሩ ብረቱ እንደተለመደው ሆኖ እጀታው ከቀንድ ይሰራል። የቀንድ ካራ/ቢላዋ የሚጠቅመው የመድሃኒት ዕፅዋት የራሱ የሆነ ጠባቂ መንፈስ አላቸው ተብሎ ስለሚታመን ለመድሃኒትነት የሚውሉ ዕፅዋት በሚቆረጡበት ሰዓት ከቀንድ የተሰራው ካራ/ቢላዋ የዕፅዋቱ ጠባቂ መንፈስ እንዳይጣላቸውና መድሃኒትነታቸውን እንዳያከሽፍባቸው ለመከላከል፤ ከሚል እምነት የመጣ እንደሆነ መሪጌታ ስሙር፣ መሪጌታ ይባቤ ያስረዳሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ/2006 ዓ.ም)።

ለምሳሌ፣ መሪጌታ ስሙርና መሪጌታ ሕላዌ ለሾተላይ በሽታ የሚያገለግለውን ዕፅ ሲቆረጡ አጥኝው በአካል ተገኝቶ ክዋኔውን ለማየት እንደሞከረው ይህን የዕፅዋት መድሃኒት ለመቁረጥ ከሚያስፈልገው ቁስ ውስጥ የቀንድ ካራ/ ቢላዋ አንዱ ነው። የቀንድ ካራው ደግሞ እንዲሁ አገልግሎት ላይ አይውልም፡፡ ድምድም ኮከን ያለው አውራ ዶሮ ተይዞ መድሃኒቱ ያለበት ቦታ ወስደው የዕፅ አንግስ ጸሎት የሆነውን "የጸሐይና የጨረቃን ሹመት ሽሬ ላንቺ ሹሜሻለሁ። የእከሌን ልጅ አስወልጅ"፣ ብለው ሶስት ጊዜ ጸሎት ካደረሱ በኋላ በተያዘው የቀንድ ካራ/ቢላዋ የአውራ ዶሮውን ኮከን በቢላዋው/ በቀንድ ካራው በማድማትና ደም በማስነካት መድሃኒቱን ከሶስት ቦታ ቆፍረው በማውጣትና አሁንም ከደሮው ደም ስሮቹ ይነኩና ስሮቹን ባንድ ላይ በቀለበት መልክ ክብ ይሰሩና ውሃ ባልነካ ሃገሬ/ ፈትል ጨርቅ ተጠቅልሎ መድሃኒቱን ነብሰ ጡር ለሆነች ሾተላይ በሽታ ላለባት ሴት ሲሰጡ በምልከታው ሂደት ለማረጋገጥ ችሏል።

ባህላዊ ሃኪሞቹ መድሃኒት ሲያዘጋጁ ከሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቁሳቁሶች ውስጥ አንዱ ወፍ ያልቀመሰው ውሃ ይጠቀሳል። "ወፍ ያልቀመሰው ውሃ" የሚባለው በሌሊት ወፍ ሳይንጫጫና ሰው ከእንቅልፉ ተነስቶ ውሃ ሳይቀዳ የሚቀዳ ውሃ ነው። ይህ ውሃ ለመድሃኒት መቀመሚያ የሚመረጥበት ምክንያት ያልረከሰ በመሆኑ በዚህ ውሃ ከተቀመመ መድሃኒቱ ፈዋሽ ይሆናል፣ ይሰራል (ይሰምራል)፤ ሲሉ መሪጌታ ኤልያስ ይገልጻሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ/2006 ዓ.ም)።

ባህላዊ መድሃኒትን በማዘጋጀት ሂደት ትክል ድንጋይ አንዱ ቁሳዊ ባህል ነው። በጥናቱ የተሳተፉ ሁሉም የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድኃኒቶች ከመቆረጣቸው በፊት በትክል ድንጋይ ላይ ሆነው የዕፅ ማንገሻ ጸሎት ይደግማሉ። የትክል ድንጋዩ አገልግሎቱም ለባህል መድሃኒት የሚቆፈሩትና የሚቆረጡት ዕፅዋቶች እንዲሰሩ ወይም እንዲሰምሩ ለማድረግ ያስችላል። ምክንያቱም በዕፅዋቱ ቆረጣና ቁፈራ ሂደት ትክል ድንጋይ ላይ ሆኖ መናፍስት ሲጠሩ ሓይልና ስልጣናቸውን ያጣሉ። በዚህም ለባህል ሃኪሙ ታዛዥ ይሆናሉ፤ የተጠየቁትንም ተግባር ይፈጽማሉ ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ያስረዳሉ።

በጥናቱ የተሳተፉ የባህል ሃኪሞች እንደ በሽታው ዓይነት ከተለያዩ የዕፅዋት ዓይነት የሚቀምሟቸውን መድሃኒቶች በአምሳያ ላም ቅቤ በመለወስ በቁስል ላይ ሲያደርጉ በጥናቱ ሂደት ለማየት ተችሏል። የአምሳያ ላም ቅቤ አገልግሎቱ የተለያዩ ዕፅዋቶች ለአንድ መድሃኒት ሲቀመሙ መድሃኒቶቹን ማዋሃድና በተጨማሪም ራሱን ችሎ በመድሃኒትነት ማገልገል ነው። በዚህ ምክንያት የአምሳያ ላም ቅቤ ሲዘጋጅ ውሃ እንዳይነካው ጥንቃቄ ይደረጋል። ምክንያቱም ውሃ ማንኛውንም ዓይነት መድሃኒት የማርከስ ሃይል ያለው ነው ተብሎ ይታመናል። የቅቤው ተምሳሌትም መድሃኒቱን የማንገስና የመድኃኒቶችን የእርስ በርስ ውህደት ለማስመር ሲባል ጥቅም ላይ እንደሚውል መሪጌታ ህላዌ፣ መሪጌታ ስሙርና መሪጌታ ኤልያስ ይገልጻሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሰኔ 2006 ዓ.ም)።

የጥቅምት ማር ወይም የእስጢፋኖስ ማር ደግሞ ሌላው በባህላዊ መድሃኒት ዝግጅት ሂደት ጥቅም የሚሰጥ ቁሳዊ ባህል ነው። የጥቅምት/ የእስጢፋኖስ ማር በዋናነት ለባህላዊ መድሃኒት ጥቅም ላይ የሚውለው ከመጽሐፍ ቅዱስ

ጋር የተያያዘ እንደሆነ መሪጌታ ስሙር ይገልጻሉ። በመጽሐፍ ቀዱስ ሃዋርያት ስራ ላይ ሰማዕቱ ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ የሞተበትና ሰማዕትነት ያገኘበት በዚህም ከፈጣሪ ቃል ኪዳን የተቀበለበት ዕለት ጥቅምት 17 በመሆኑ በዚህ ዕለት የተቆረጠ ማር የሚሰምር ወይም ለመድሃኒትነት ማገልገል የሚችል በመሆኑ ነው፤ በማለት ገልጸዋል (ቀለ መጠይቅ፣ ሃምሌ/2006 ዓ.ም)። ከዕለታት ውስጥ ደግሞ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ አርብና ቅዳሜ ለባህል መድሃኒት መቁረጫ፣ መቆፈሪያና ማዘጋጃ ቀናት በመሆን ያገለግላሉ።

በአጠቃላይ ከባህል ህክምና ባለሙያዎች ከቃለ መጠይቅና ከምልከታ ከተገኙ መረጃዎች መገንዘብ የሚቻለው ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒትን በማዘጋጀት ሂደት የመድሃኒት ዕፅዋቱን ከመሰብሰብ ጀምሮ ቀምሞና አዘጋጅቶ ለበሽተኛው እስከሚሰጥበት ደረጃ ድረስ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ ቁሳቁሶች ጥቅም ላይ የሚውሉ መሆኑን ነው። ከእነዚህ ቁሳዊ ባህሎች በተጨማሪ ባህላዊ መድኃኒቶች ሲዘጋጁ መድሃኒቶቹን ለማዋሃድና ለመቀመም የሚያገለግለሉ ቁሳዊ ባህሎችም ውስጥ እንደ የጥቅምት ወይም የእስጢፋኖስ ማር፣ ወፍ ያልቀመሰው ውሃና የአምሳያ ላም ቅቤ የመሳሰሉት መድሃኒትን በመቀመም ሂደት ለማዋሃጃነት ከማገልገላቸውም በላይ ራሳቸውን ችለው እንደ ባህላዊ መድኃኒትም የሚያገለግሉ ናቸው። የመድኃኒት ዕፅዋቱ ፈዋሽ እንዲሆኑ የሚሰበሰቡትም፣ እህል ሳይቀመስ በባዶ ሆድ፣ ሽንት ቤት ሳይወጣና ከማንም ጋር ወሬ ሳይወራ ሲሆን፣ የባህላዊ መድሃኒቱን ለመሰብሰብም፤ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ዓርብና ቅዳሜ ዕለታት ወሳኝ እንደሆኑና እነሱም ባህላዊ መድሃኒቱ ፍቱንና ፈውስ ሰጭ መድሃኒት እንዲሆኑ ያስችላሉ ተብሎ እንደሚታመን ከመስክ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

## የባህል መድሃኒት ቅመማና አሰጣጥ

### የባህል መድሃኒት ቅመማ

በባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ዝግጅትና ቅመማ ሂደት አብዛኛዎቹ ዕፅዋቶች ብቻቸውን ለመድሃኒትነት አይውሉም። ከላይ በባህላዊ መድሃኒት ዝግጅት ሂደት የሚያገለግሉ ቁሳዊ ባህሎችን ባየንበት ክፍል እንደተገለጸው የባህላዊ መድሃኒት የዕፅዋት ግብዓቶች በመድሃኒት ዝግጅት ወይም ቅመማ ሂደት ውሃ ባልነካ ቅቤ፣ በእስጢፋኖስ ማር፣ ወፍ ባልቀመሰው ውሃ በማዋሃድ እየተቀመሙ ለበሽተኛ ይሰጣሉ።

ለምሳሌ፣ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ መሪጌታ ስቡህ እና መሪጌታ ኤልያስ እንደገለጹት "ለችፌ በሽታ፤ የሁለገብ፣ የአቱች ቅጠል፣ የአንተርፋ፣ የድግጣ/ ዝግጣ፣ የኮሶ ፍሬና ቅጠል በአንድ ላይ ደቁሶ ዉሃ ባልነካ ቅቤ መቀመም አንደኛው ዘዴ መሆኑን ይገልጻሉ። መሪጌታ ህላዌና መሪጌታ ስቡህ ደግሞ የበለስ ቅጠል፣ የጥቁር አዞ ሃረግ፣ የአክማ አበባና ቅጠል፣ የእንዝርዘይ አበባ፣ የነጩ አዞ ሃረግ ቅጠል ባንድ ላይ ወይም ከእነዚህ ውስጥ የተገኙትን ሰብስቦና ወቅጦ ቁስሉን እያጠቡ በእስጢፋኖስ/ በጥቅምት ማር ለውሶ መቀመም መድሃኒትነቱ ፍቱን እደሆነ ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ /2006 ዓ.ም)። ከዚህ በተጨማሪ መሪጌታ ህላዌና መሪጌታ ይባቤ ደግሞ፤ የደጋ አባሎ ፍሬና ቅጠል፣ የቁልቋል አበባ ከተሰበሰባና ከተወቀጠ በኋላ ቁስሉን በመጀመሪያ በሽንት በደንብ አጥቦ በማዘጋጀት መቀመም ተገቢ ነው። ይህ መድሃኒት ቁስሉን በመጀመሪያ አቁስሎና አነፍርቆ መልሶ ያድናል፤ በማለት ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ /2006ዓ.ም)።

### የባህል መድሃኒት አሰጣጥ

በጥናቱ የተሳተፉ የባህል ሐኪሞች ያዘጋጁቸውን ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቶች ለበሽተኞቹ ለማዘጋጀትና ለመስጠት በቅድሚያ የበሽተኛው እድሜ፣ ፆታ፣ በሽተኛው ያለበት ሁኔታ፣ በሽተኛው የደረሰበትን ጉዳት፣ በሽታው በአካል ላይ የተከሰተበትን ሁኔታ መሰረት በማድረግ የበሽታውን ዓይነት ከለዩ በኋላ ባህላዊ መድሃኒቱን በማዘጋጀት ይሰጣሉ።

እንደ መሪጌታ ስሙር፣ መሪጌታ ስቡህ፣ መሪጌታ ህላዌ ገለጻና እና ከምልከታ ከተገኘው መረጃ መረዳት የሚቻለው በሽታው ከተለየና መድሃኒቶቹ ከተቀመሙ በኋላ እንደበሽታው ዓይነት፤ በሚቀባ፣ በሚሸተት፣ በሚታጠንና በሚጨስ፣ በሚነሰነስ፣ በሚታሰር፣ በሚታኘክና በሚቆረጠም፣ በሚጠጣ፣ በሚበላ እና በመሳሰሉት ይሰጣሉ። በተጨማሪም የባህል ሃኪሞቹ ለበሽተኛው የሚሰጠው መድሃኒት መቼ፣ እንዴት፣ ስንት ጊዜ፣ በምን መንገድ እንደሚወሰድ፣ እንደሚቀባ፣ ምን ምግብ መበላት እንዳለበትና እንደሌለበት፣ ከምን ከምን ነገሮች መቆጠብ እንደሚባ ያብራራሉ። ምክንያቱም ባህላዊ መድሃኒቶች የተለያየ ባህርይ ያላቸው በመሆኑ ለበሽተኛው የተሰጠው መድሃኒት የሚጎዳና የሚያዳክም ሊሆን ስለሚችል የማርከሻውን/ የመመለሻውን ምንነት ከግልጽ ማስጠንቀቂያ ጋር መድሃኒት እንደሚሰጡ በመስክ ጥናቱ ሂደት አጥኝው ለማረጋገጥ ችሏል።

በተጨማሪም በጥናቱ ሂደት የተሳተፉ በጎንደር ከተማና አካባቢ የሚገኙ የባህል ሃኪሞች በመጀመሪያ ደረጃ

የበሽተኛውን ሁኔታና የበሽታው ዓይነት ከተገነዘቡ በኋላ እንደመድሃኒቶቹ ባህርይ በማንኪያ፣ በፍንጃል፣ በብርጭቆ፣ በብርሌ፣ በዋንጫና በመሳሰሉት መለኪያዎች መጥነው ይሰጣሉ። እንዲሁም ህመምተኞች መድሃኒት ሲወስዱ፣ ከወሰዱ በኋላና እስከሚድኑ ድረስ ከተለያዩ ነገሮች እንደሚከለከሉና ሌሎች አካላት ጋር መገናኘት እንደማይፈቀድና የሚከውኗቸው ልማዳዊ ድርጊቶች እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል። በመስክ ቆይታ የባህል ሃኪሞቹ ደንበኞቻቸው ህሙማን፤ ከጥላ (ከፆታዊ ግንኙነት)፣ ከአልኮል፣ ከሰው አይነጥላ መታቀብ እንዳለባቸው ገልፀዋል። ምክንያቱም እነዚህ ጉዳዮች ህመምተኛ የማዳከም፣ መድሃኒት የማርከስ፣ በሽታው እንዲጠነክር የማድረግ ባህርይ ሊኖራቸው ስለሚችል እንደሆነ መሪጌታ ህላዌ፣ መሪጌታ ስሙር፣ መሪጌታ ይባቤና መሪጌታ ኤልያስ ይገልጻሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ /2006ዓ.ም)።

በአጠቃላይ የባህል ሐኪሞች መድሃኒት ለመስጠት በመጀመሪያ ደረጃ የበሽታው ዓይነት፣ የህመምተኛውን ሁኔታ ማለትም አቅም፣ እድሜና ጾታን መሰረት በማድረግ በሽታውን እንደሚለዩና ለዚሁ ተግባር የሚያገለግሉ ባህላዊ የዕፅዋት ዓይነቶችን የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመጠቀም እንደሚቆርጡ፣ እንደሚቆፍሩና እንደሚያዘጋጁ፣ ባህላዊ መድሃኒቱን እንደሚሰጡና በሽተኛው ደግሞ መድሃኒቱን ከወሰደ በኋላ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው እና ታካሚዎች ከህመማቸው እስኪድኑ ድረስ ከጥላ፣ ከአልኮል፣ ከፆታዊ ግንኙነትና ከመሳሰሉት ነገሮች ተቆጥበው ወይም ተገልለው መቀመጥ እንዳለባቸው ከጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

### የባህል ህክምና ጥበብ ምስጢራዊነት፣ የመተላለፊያ መንገድና የማህበረሰቡ አመለካከት

በጥናቱ ሂደት ለማየት እንደተሞከረው፣ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ጥበብ ድብቅና ምስጢራዊ ነው። ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ምስጢራዊ የመሆኑ ምክንያት ደግሞ የህክምና እውቀቱ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፍና ጥበቡ ከጊዜ ጊዜ እየጠፋ እንዲሄድ አስተዋፅኦ አድርጓል። ከመስክ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ባህላዊ ህክምና ጥበብ ምስጢራዊ የሆኑበት ምክንያት ለመድሃኒት የሚያገለግሉ ዕፆች እንዳይጠፉና እንዲጠበቁ፣ የታካሚውን ስነልቦና ለመጠበቅ፣ የባህላዊ ሃኪሞቹን ባለቤትነት ለማረጋገጥና ከማህበረሰቡ የሚያገኙት ኢኮኖሚያዊና ሞራላዊ ጠቀሜታ (በማህበረሰቡ ዘንድ ተከብሮ የመኖርን) ለማስጠበቅ፣ እንዳይራከሱ፣ መድሃኒቶቹ በየቦታው የሚገኙ በመሆናቸው ሰው እየነቀለ እንዳያጠፋቸው ለማድረግ እንደሆነ በጥናቱ የቡድን ውይየት የተሳተፉ አብዛኛዎቹ መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ ዕፅዋት በቀላሉ የማይገኙ በመሆናቸው ከምድረ ገጽ እንዳይጠፉም እንደሚያግዝ የባህል ሃኪሞቹ ይገልጻሉ። እንዲሁም ባህላዊ መድሃኒት በተገቢው መንገድ ካልተያዘ ሰው ባላጋራውን ሊገድልበት ወይም ራሱን ሊያጠፋበት ይችላል። ባጠቃላይ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒቶች እንዳይጠፉና ለአሉታዊ አገልግሎት እንዳይውሉ ለመከላከል እንደሆነ መሪጌታ ኤልያስ፣ መሪጌታ ስሙር፣ መሪጌታ ህላዌ፣ መሪጌታ ኤልያስ፣ መሪጌታ ይባቤ እና መሪጌታ ስቡህ ይገልጻሉ(ቃለ መጠይቅ፣ ሐምሌ /2006ዓ.ም)።

ከዚህ በተጨማሪ አጥኝው ባደረገው ምልከታ ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት ከላይ ከተገለጹት ጠቀሜታዎች በተጨማሪ መከበሪያና መፈሪያ ናቸው። በመሆናቸውም የባህል ሃኪሞቹን ማንም አካል እንደማይቃወማቸው ለመረዳት ተችሏል። ማህበረሰቡም የባህላዊ የዕጽዋት መድሃኒትን ፈዋሽነት ቢያምንበትም ባህላዊ መድሃኒት መጠቀም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሌለውና የሚያስወግዝ ተግባር በመሆኑ አብዛኛዎቹ ባህላዊ መድሃኒት ተጠቃሚዎች መድሃቱን በድብቅ እንደሚወስዱና ባህላዊ ሃኪሞችም ቢሆን ተግባሩ የሚያስወግዛቸው በመሆኑ ድርጊቱን ለሌላ አካል ግልጽ ባለማድረግ ሲሰሩ ማየቱ ከላይ ለተባለው ሃሳብ በመረጃነት ሊጠቀስ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ አብዛኛዎቹ መድሃኒት አዋቂዎች በተለያየ ምክንያት ከዚህ ዓለም ሲሞቱ የባህል መድሃኒቱን ለተተኪው ትውልድ ሳያስተላልፉ እውቀቱን እንደያዙት እንደሚቀበሩ በጥናቱ ሂደት ከተሳተፉ የባህል መድሃኒት አዋቂዎች ገለጻ ያስረዳል።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ በቀረቡት ምክንያቶች ማህበረሰቡ ለባህላዊ የዕጽዋት መድሃኒት ያለው አመለካከት ከዘመናዊው ህክምና ባልተናነሰ ጥሩ አመለካከት ያለው ቢሆንም ከማህበረሰቡ አሉታዊ አመለካከት የተነሳና ከባህል መድሃኒት አዋቂዎች ግላዊ መብት ጋር በተያያዘ ባህላዊ መድሃኒቶች ተስተላልፏቸው ምስጢራዊ እንዲሆን፣ ተስተላልፎው ዝቅተኛ በመሆኑም ተተኪ ትውልድ እንዲጠፋ፣ ሀገሪቱ በባህላዊ ህክምናው ዘርፍ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንዳታገኝም ያደረገ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የባህል ሃኪሞች ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት አቀማመም፤ አዘገጃጀት፣ በሽታ የመለያ ዘዴና አሰጣጥን መመርመር ሲሆን፣ ጥናቱ የተካሄደበት ቦታም ጎንደር ከተማና አካባቢ በሚገኙ ስምንት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሆኖ በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የተመረጡ ስምንት የባህል ሀኪሞች መረጃ ተሰብስቦባቸዋል። ጥናቱ ከቀዳማይ የመረጃ ምንጮች የሚገኙ መረጃዎችን በቃለመጠይቅ፣ በተሣትፏዊ ምልከታ ደግሞ የመድኃኒት

ዕፅዋቱ የሚገኙበት ቦታ ድረስ በመሄድ ከዕፅዋትና ከዕፅዋት ተዋፅኦዎች ናሙና ሲሰበሰብና የትኛው አካላቸው ለመድኃኒትነት እንደሚውል፤ በታላሚ የቡድን ውይይት ደግሞ በዕፅዋት አሰባሰብ ወቅት ጥቅም ላይ የዋሉ ቁሳቁሶችና ባህላዊ ሃኪሞቹ ዕፅዋቱን ሲሰበስቡ የሚከውኑትን ስርዓት ገቢርና የሚጸልዩትን የዕፅ ማንገሻ ጸሎት ምንነት፤ ፋይዳና ትዕምርታዊነት/ተምሳሌታዊነት ለማየት ተችሏል። ለጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎችንም በትክክልና ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ በማደራጀትና በማጣራት በገላጭና በይዘት የመረጃ መተንተኛ ስልት ተተንትነዋል።

በጥናቱ ሂደት በመረጃ ትንተናው አጥኝው ለማረጋገጥ እንደሞከረው፦

- የባህል ሃኪሞች ባህላዊ መድሃኒት ለማዘጋጀት ሲሉ የተለያ ዕፅዋቶችን፣ የዕፅዋቶቹን ስር፣ ቅጠል፣ ቅርፊት፣ አበባ፣ ፍሬና የመሳሰሉ የዕፅዋቶቹን ክፍሎች በግብአትነት እንደሚጠቀሙና እነዚህን እፅዋቶችም እህል ሳይቀምሱ በባዶ ሆድ፣ ሽንት ቤት ሳይጠቀሙና ከማንም ጋር ወሬ ሳያወሩ እንደሚሰበስቡ፤
- የባህል መድሃኒት አዋቂዎች የባህል መድሃኒቱን፤ ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ ዓርብና ቅዳሜ ደግሞ የዕፅዋቱ መቁረጫ፣ መቆፈሪያና መቀመሚያ ዕለታት እንደሆኑና በእነዚህ ዕለታት ዕፅዋቱ የሚቆረጡበት ምክንያት ሐይማኖታዊ ይዘት ያለውና መድሃኒቱ እንዲሰምር የሚያደርጉ መሆኑን፤
- ባህላዊ መድኃኒቶችን ለማዋሃድና ለመቀመም የሚያገለግሉ ወፍ ያልቀመሰው ውሃ፣ የጥቅምት ማር፣ ውሃ ያልነካውና የአምሳያ ላም ቅቤም ለመድሃኒትነት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ፤
- የባህል ሐኪሞች መድኃኒት ለመሰብሰብና ለበሽተኛው ለመስጠት በመጀመሪያ ደረጃ የበሽታው ዓይነት፣ የህመምተኛውን ሁኔታ ማለትም አቅም፣ እድሜና ጾታን መሰረት በማድረግ ባህላዊ በሆነ መንገድ በሽታውን እንደሚለዩ፤
- ለባህላዊ መድሀኒትነት የሚያገልግሉ ባህላዊ የዕጽዋት ዓይነቶችን የተለያዩ ቁሳዊ ባህሎችን በመጠቀም እንደሚቆርጡ፣ እንደሚቆፍሩ፣ እንደሚያዘጋጁ፣ እንደሚሰጡና እነዚህ ቁሳዊ ባህሎች ደግሞ የተለያየ ተምሳሌታዊ ትርጉም ያላቸውና ለመድሃኒቱ ፍቱን መሆን የራሳቸው አስተዋጽኦ ያላቸው ናቸው ተብሎ እንደሚታመኑ፤
- በሽተኛዎቹ መድሃኒቱን ከወሰዱ በኋላ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለባቸው እና ታካሚዎች ከህመማቸው እስኪድኑ ድረስ ከጥላ፣ ከአልኮል፣ ከፆታዊ ግንኙነትና ከመሳሰሉት ነገሮች ተቆጥበው ወይም ተገልለው እንደሚቀመጡ፤
- እጅግ ትልቅ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው የባህል መድሃኒቶች አሁን አሁን በማህበረሰቡ ዘንድ መጠቀሙ እየቀረ እና ሙያውም ከትውልድ ወደ ትውልድ የመተላለፉ ጉዳይ በአብዛኛው ምስጢራዊ በመሆኑ የመጥፋት አደጋ የተደቀነባቸው እንደሆነ፤
- ባህላዊ ሃኪሞችና የባህል መድሃት ተጠቃሚዎች የዕፅዋት መድሃኒት በህክምና ያማይድኑ በሽታዎችን ጨምሮ በመፈወስ ረገድ የተሻሉ እንደሆኑ እንደሚያምኑ ማየት ተችሏል።

## *ይሁንታ*

ከላይ ከተጠቀሱት የጥናቱ ግኝቶች በመነሳት ጥናቱ የሚከተሉትን የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበዋል።

- የባህል ሐኪሞች ባህላዊ በሆነ መንገድ የበሽታውን ዓይነት በመለየት መድሃኒት የሚሰጡ በመሆናቸውና ድርጊቱ ተጠቃሚዎችን ለከፋ አደጋ የሚዳርግ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ለባህል መድሃኒት አዋቂዎች ስልጠና በመስጠት ባለሙያዎቹ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ የባህላዊ ህክምና ተግባር እንዲያከናውኑ ቢደረግ፤
- ባህላዊ የዕፅዋት መድሃኒት በባህላዊ መንገድ ሲዘጋጅ ባህላዊ መንገድን የተከተለ በመሆኑ የመድሃኒት ዕፅዋቱ የመጥፋት አደጋ ተጋርጦባቸዋል፡፡ ስለዚህ የሚመለከታቸው አካላት ከባህል መድሃኒት አዋቂዎች ጋር በመወያየትና ስልጠና በመስጠት ዘመናዊ የሆነ አሰራርን በመዘርጋት የመድሃኒት ዕፅዋቱ ከጥፋት የሚድኑበት መንገድ ቢተኮርበት፤
- የባህላዊ መድሃኒቶች በአብዛኛው ምስጢራዊ በሆነ መንገድ አገልግሎት የሚሰጡ በመሆናቸውና በሽተኛዎቹ መድሃኒቱን ከወሰዱ በኋላ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ታካሚዎች ለተለያዩ አደጋዎች ሊጋለጡ ስለሚችሉ ለባህል መድሃኒት አዋቂዎች ስልጠና የሚሰጥበትንና በዘመናዊው ህክምና ከሰለጠኑ ባለሙያዎች ጋር በጋራ የሚሰሩበት ሁኔታ ቢፈጠር፤
- የዕፅዋት መድሃኒት በህክምና ያማይድኑ በሽታዎችንም ጨምሮ በመፈወስ ረገድ የተሻሉ እንደሆኑ ተጠቃሚዎቹና ባህላዊ ሃኪሞች እንደሚያምኑና አጥኝውም በምልከታው ያረጋገጠው ሁኔታ በመኖሩ ሰፋ ያለ ፕሮጀክት ቢቀረጽና ዩኒቨርሲቲውን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ለአጥኝዎቹ ድጋፍ ቢያደርጉና የመድሃኒቱን ንጥረ ነገር በማጥናት ለሀገራዊ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበት መንገድ ቢመቻች፤
- እጅግ ትልቅ ሃገራዊ ፋይዳ ያላቸው የባህል መድሃኒቶች አሁን አሁን በማህበረሰቡ ዘንድ መጠቀሙ እየቀረ እና በዚያው ልክ ደግሞ ሙያው ከትውልድ ወደ ትውልድ የመተላለፉ ነገር አደጋ ውስጥ እየገባ በመሆኑ ቀጣይ

ጥናቶች እየተካሄዱና ወደ ቴክኖሎጅ ሽግግር ፕሮጀክት እየተቀየሩ የሚስፋፉበት ሁኔታ ቢፈጠር ኒቨርሲቲው ብሎም ሀገሪቱ ከባህል መድሃኒት ማግኘት የሚገባትን ጥቅም ልታገኝ የምትችል መሆኑን አጥኝው ይጠቁማል

## ዋቢ ጽሑፎች


መስፍን ፈቃዴ። (2002)።"የባህላዊ መድሃኒት አዘገጃጀት በደብረ ማርቆስና አካባቢው፡፡"ኤምኤ ቴሲስ፣ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ አ.አ.ዩ፡፡

አማን በላይ። (2006)። መጽሐፈ አድህኖት ጥቅሙ ሙሉ ጤና ለሁሉ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

በቀለች ቶላ፡፡ (2007)። ሕክምና በቤታችን። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ተመስገን በየነ፡፡ (2003)።"በባህላዊ ህክምና በሽታን የመለያ ዘዴ፣ የመድኃኒት ቅመማና አሰጣጥ በራቤል ወረዳ"። ኤምኤ ቴሲስ፣ የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ አ.አ.ዩ።

Abera Geyid. (2003). "Traditional Medicine in Ethiopia." *Proceeding of a National Workshop*: Held In Addis Ababa, 30 June-2July.

Agonafir.E. (2004)."Vision and Mission of Traditional Health Practitioners in Ethiopia." In Urga. K, Assefa. A, and Guta. M, (eds). *Traditional Medicine in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute*: Addis Ababa, PP. 48-51.

Alemayehu Moges. (1984). "Traditional Ethiopian Medicines." Institute of Ethiopian S tudies; Eight International Conferences of Ethiopian Studies: Addis Ababa University.

Dawit Abebe (1996) (ed). Development and Utilization of Herbal Remedies in Ethiopia. Ethiopian Health and Nutrition Research Institute: Addis Ababa.

Fekadu Fullas. (2001). Ethiopian Traditional Medicine: Common Medicinal Plants in Perspective. Sioux City Lowa: St. Luke's Regional Medical Center.

Konadu, Kwasi.(2007). Indigenous Medicine and Knowledge in African Society. New York and London: Taylore and Francis Group PLC.

National Center for Farmworker Health.(2011). Folk Medicine and Traditional Healing. Np: August.

Sofowora, Abayomi.(1982). Medicinal Plants and Traditional Medicine in Africa. New York: John Wiley and Sons Ltd.

Wondwoson Teshome. (1999). "Indigenous Medicinal Plants Used in Ethiopia" *Viennese Ethno medicine News Letter*; vol.9,No.2:PP.28-32.

WHO.(2002). Traditional Medicine Strategy 2002-2005. Geneva; Renata Kerr: Printed in France.

Yoder, Don.(1972). "Folk Medicine" In Richard Dorson (ed). *Folklore and Folk life; An Introduction*. Chicago, London: University of Chicago Press: PP. 190-214.

Young, Allan Louis. (1970). Medical Beliefs and Practices of Begemder Amhara. Published PHD Dissertation in Philadelphia: University of Pensylvania.